# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ስርቆት እና ወረራ የፈተነው ደቡብ ምዕራብ ሪጅን

አስናቀ ፀጋዬ

የደቡብ ምዕራብ ሪጅን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ስድስቱንም ዞኖችን፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የየም ዞንን፣ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞንን፣ ቡኖ በደሌን፣ ኢሊባቦር ዞንን እንዲሁም በጋምቤላ ክልል ያሉ ሁሉንም ዞኖችን የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰጥ በስሩ 11 ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች ያሉት ነው። ከጊቤ አንድና ሁለት እንዲሁም ከፊንጫ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቀርብለት የደቡብ ምዕራብ ሪጅን 13 ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ያሉት ሲሆን ከ132 እስከ 400 ኪሎ ቮልት መስመሮችን ያስተዳድራል። 1 ሺህ 900 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሰርኪዩት መስመር፣ የፍተሻ ጥገና፣ ኦፕሬሽን ይሠራል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የደቡብ ምዕራብ ሪጅን ኃይል ማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፈያ ጣቢያ ኦፕሬሽን መምሪያ ዳይሬክተር አቶ ጌታሁን ሲሳይ እንደሚሉት የደቡብ ምዕራብ ሪጅን በ11 የኃይል ማከፋፊያ ጣቢያዎቹ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚያገኙ 11 ጣቢያዎች አሉ። ከሪጅኑ ኃይል ተቀብለው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚተዳደሩ ለምሳሌ ከሚዛን ወደ ቴፒ የተዘረጋ ቴፒ አካባቢ አገልግሎት የሚሰጥና ከጋምቤላ ደግሞ ወደ ደምቢዶሎ የተዘረጋ ለቄለም ወለጋ አካባቢ የሚሰጥ መስመሮች አሉ። ባጠቃላይ በሪጅኑ በጣቢያ ደረጃ ከሚሰጠው ኃይል በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሦስት ንዑስ ጣቢያዎችን ያስተዳድራል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚዘረጉ መስመሮች እንዳሉ ሆነው ለደቡብ ምዕራብ ሪጅን ከጊቢ አንድና ሁለት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨ ኃይል ስለሚቀርብ እንዲሁም በበደሌ ከፊንጫ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨ ኃይል ስለሚገኝ ብሎም የኃይል ትስስሩም ከዋናው የኤሌክትሪክ ኃይል ቋት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ሪጅኑ የኃይል አቅርቦት ችግር የለበትም።

ዳይሬክተሩ እንደሚያብራሩት በሪጅኑ በኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ላይ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች አሉ። በተለይ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ማማዎች ብረት ስርቆት ጋር በተያያዘ ተደጋጋሚ ችግሮች ያጋጥማሉ። ከዚህ ችግር ጋር በተገናኘ ለምሳሌ በዚህ ዓመት በደሌ መቱ ላይ አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ገመድ ተሸካሚ ማማ ወድቋል። በሌላ በኩል ከካሣ ጋር በተገናኘ ኅብረተሰቡ የካሣ ይገባኛል ጥያቄ በተለያየ መልኩ ያቀርባል። ከዚህ በፊት ሲከፈል የነበረው የካሣ ክፍያ አግባብ አይደለም፤ ፕሮጀክቱ ከተሠራ አስር ዓመት ስላለፈው እንደ አዲስ ካሣ ይከፈለኝ የሚሉ ጥያቄዎችን በመቅረባቸው መስመሩን ለመፈተሽ እንቅፋት ፈጥሯል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በዋና ሥራ አስፈፃሚ ስር የመሠረተ ልማቶች ቁጥጥርና ክትትል ክፍል ተቋቁሞ ከደኅንነት ቢሮዎች ጋር፣ ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳዎች ጋር በመሆን ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ሪጅኑም ስርቆት በሚበዛባቸው አካባቢዎች በተለይ ቡኖ በደሌና መቱ ላይ ስብሰባ በማድረግ ዞኖች ለወረዳ መርተው ወረዳዎች ደግሞ ፖሊስ መድበው ችግር ያለባቸው መስመሮች እንዲፈተሹና በዚህ የስርቆት ድርጊት የተሳተፉ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም። ምንም እንኳን ስርቆቱ በፊት ከነበረው ሁኔታ በአንፃራዊነት የቀነሰ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ መቆም አለበት።

የደቡብ ምዕራብ ሪጅን ኃይል ማስተላለፊያ ባሉት 11 ጣቢያዎች የማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት አንደኛ ጅማ ሁለት ላይ ለመሠረተ ልማቱ ተብለው ለተነሱ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። 50 አባወራዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በቅተዋል። ለዚህ ሥራም ወደ 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ተፈፅሟል።



አቶ ጌታሁን ሲሳይ

በተጨማሪም ግልገል ግቤ በሶኮሩ ንኡስ ጣቢያ ላይ የተነሱ ሰዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ በተመሳሳይ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ተፈፅሟል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራውን እስካሁን አልጀመረም። እዚሁ አካባቢ ላሉ ሰዎች የውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ ለወረዳው ክፍያ ተፈፅሟል። ሆኖም ወረዳው ሥራውን እስካሁን አልጀመረም።

ዳይሬክተሩ እንደሚናገሩት ከዚህ በፊት የነበሩ በጣም ቅሬታ የነበረባቸው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትንም፤ ኅብረተሰቡንም የተሻለ አገልግሎት እየሰጡ ያልነበሩ የ33 እና የ15 ኪሎ ባይት መስመሮች ከተለያዩ ጣቢያዎች ይወጣሉ። አገልግሎቱ ለኅብረተሰቡ የሚደርሰው በዚህ አማካኝነት ስለሆነ በሪጅኑ የበደሌ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በኃይል መቆራረጥና ረገድ በጣም ችግር ያለበትና በጥገናም በተደጋጋሚ ምልልስ የሚበዛበት አካባቢ ስለነበር ይህን በመቀየር ያልተቆራረጠ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላ ሁለቱም መስመሮች እስካሁን በተሻለ ሁኔታ የኃይል አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል ጅማ አንድ ግልገል ጊቤ አንድ መቱ ኃይል ማከፋፋያ ሦስት ጣቢያዎች ላይ የሲቪል ሥራዎች ተጀምረዋል። የጊቤ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሞባይል ሰብ ስቴሽን መጥቶ ተቀይሮ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። የሌሎቹ ግን የሲቪል ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ነባሩን ወደ ጊዜያዊ የማዞር ሥራ የጅማ፤ የመቱ ደግሞ የቁጥጥር ክፍል ሥራ ቁፋሮ አልቆ ብረትና ሲሚንቶ ገብቶ አልቋል። ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሲቪል ማሻሻያ ሥራዎቹ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይታሰባል።

የደቡብ ምዕራብ ሪጅን ዋነኛ ደንበኛ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆን ከሪጅኑ ቀጥታ አገልግሎት የሚያገኙም ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሆስፒታሎችና ፋብሪካዎች አሉ። ሪጅኑ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በኦፕሬሽን፣ መስመሮች ሲቋረጡና ሌሎች ችግሮችም ሲፈጠሩ የዕለት ተዕለት ግንኙነት አለው።

የሪጅኑ አሁናዊ አንገብጋቢ ጉዳይ ከኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ተሸካሚ ማማ ብረት ስርቆት ጋር ያለው ችግር ነው። ይህ ስርቆት መቆም ይኖርበታል። ጠንከር ያለ ሕግ እስካልወጣ ድረስ ይህ ድርጊት በዚሁ ሊቀጥል ይችላል። ከዚህ አንፃር አስተማሪና ተመጣጣኝ የሆነ የሕግ እርምጃ በአጥፊዎች ላይ ሊወሰድ ይገባል። ኅብረተሰቡም እነዚህን አጥፊዎች በማጋለጥ ረገድ ንቁ ተባባሪ መሆን አለበት። በሌላ በኩል ለማስፋፊያ ተብሎ ሪጅኑ የያዛቸው ቦታዎች ካርታ ያላቸውና ክፍያም የሚፈፅምባቸው ቢሆኑም በየጊዜው በተለያዩ አካላት እየተወሰዱና እየተወረሩ በመሆናቸው ቦታውን የማስከበር ሥራ በሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደር አካላት ሊሠራ ይገባል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ